# የፀረ ሙስና ህጎች

**በፌዴራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል የተዘጋጀ 2004 ዓ.ም**

# ክፍል አንድ

## የሙስና ወንጀል ምንነትና ልዩ ባህሪያት፣

### 1. የሙስና ወንጀል ምንነት፣

የሙስና ወንጀል አፈጻጸም ከአገር አገር፣ ከቦታ ቦታ እና ከባህል ባህል የሚለያይ በመሆኑ በተለያዩ ምሁራን የተለያየ ትርጉም ሲሰጠዉ ይስተዋላል፡፡ በዚህም የተነሳ የተለያዩ ፀሀፊዎች ስለሙስና ምንንት የተለያየ ትርጉም ሰጥተዋል፤ ሁሉንም ትርጉሞች መተንተን የጽሁፉ አላማ ባይሆንም ለማሳያ ያህል የተወሰኑት እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፣

- ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠ ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል ነዉ (ትራንስፓረንሲ ኢንተረናሽናል) ፤
- ሙስና ማለት አደራን አለመጠበቅ፣እምነት ማጉደል ወይም አለመታመን፣በጉቡ በምልጃና በአድሎ ሀቅን፣ዉሳኔን ወይም ፍትህን ማዛበት ነዉ (ብላክስ ሎዉ መዝገበ ቃላት)፤
- ሙስና ማለት ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል ስርዐቶችን፣ ህጎችን፣ደንቦችን፣ አሰራሮችን ወይም/እና መርሆዎችን የመጣስ ማንኛዉም ተግባር ነዉ (የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ 1993)፤
- ሙስና ማለት በግል ወይም በቡድን፣ በፖለቲካ መሪዎች ወይም በቢሮክራቶች ስልጣንና ሀላፊነትን መከታ በማድረግ የህዝብን ጥቅምና ፍላጎት ለግል ጥቅም የማዋል ኢ-ስነምግባርዊ ድርጊት ሲሆን፤በመንግስትና የህዝብ ሀብትና ንብረት ላይ ስርቆት፣ ዝርፊያ እና ማጭበርበር መፈፀም፤ህግና ስርዐትን በመጣስ በዝምድና፣በትዉዉቅ፣በፖለቲካ ወገንተኝነት፣ በጎሰኝነት፣በሀይማኖት ትስስር ላይ ተመርኩዞ አድሎ መፈፀም፣ፍትህን ማጓደል እና ስልጣንና ሀላፊነትን አላግባብ በመጠቀም ህገወጥ ጥቅም ማግኛ ነዉ (ኬምቤሮናልድና ሰርቦረዌል 2000)፤

## 2. የሙስና መንስኤዎች

ሙስና እንዲፈጠርና እንዲስፋፋ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ምክንያቶች አሉ፣የተወሰኑትን ለማየት ያህል፡-

### 2.1. ከሰዎች አመለካከት/ባህሪ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣

ሰዎች የተለያየ ባህሪ ያላቸዉ መሆኑ ግልጽነዉ፣ስስት ሁሉም ነገር ለኔ ባይነት፣ሳይሰሩ በአቋራጭ ለመበልጸግ መፈለግ፣በአጠቃላይ ከመልካም ስነምግባር ዉጭ መሆን ለሙስና መፈጠርና መስፋፋት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፣

### 2.2. ከህግ ማዕቀፍ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

የወንጀል ህግ አንዱ ዋነኛ አላማና ግብ ለጠቅላላዉ ትቅም ሲባል አገሪቱን መንግስት፤የህዝቦቿን፤የነዋሪዎቹን፣ሰላም፣ደህንነት፣ስርዓት፣መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ሲሆን፤ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸዉ በቅድሚያ በማስጠንቀቅ፣ማስጠንቀቂያዉ በቂ ባልሆነበት ጊዜ አጥፊዎችን በመቅጣት ከጥፋታቸዉ እንዲማሩ ማድረግና ለሌሎችም ማስተማሪያ እንዲሆኑ በማድረግ ወንጀልን መከላከል ነዉ፡፡ይህ አዉን ይሆን (ሙስናን መዋጋትና አጥፊዎችን ማስቀጣት) ዘንድ የሙስና ድርጊትን ወንጀል የሚያደርጉና ለወንጀሉ ተመጣጣኝ ቅጣትን የሚጥሉ ህጎች ሊኖሩ የግድ ይላል፡፡የተሟላ ህግ ከሌለ ለሙስና በር ይከፍታል፡፡

### 2.3.ከተጠያቂነት ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

ተጠያቂነት ከሌለ ማንም ሰዉ ያሻዉንና የፈቀደዉን እንዲሰራ ምክንያት ይሆናል፡፡አንድ ሰዉ ያሻዉን ሲሰራ የማይጠየቅ ወይም ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነ ደግሞ ሙስና ይከሰታል፡፡

## 3. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪያት፣

ወንጀል በአንድ ተወሰነ የህብረተሰብ የእድገት ደረጃ እንደተፈጠረና ከህብረተሰብ እድገት ጋር እያደገና እየተወሳሰበ እንደመጣ ይታመናል፣በተለይም በአዉሮፓ ከነበረዉ

የኢንዱስትሪ አብዮት ቦኂላ ከዚህ በፊት ከሚታወቁት ወንጀሎች ሌት ያሉ ወንጀሎች እንደተፈተሩ ነገራል፣የሙስና ወንጀልም ከነዚህ አንዱ ነዉ፡፡

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች (ለምሳሌ ስርቆት፣ ድብደባ፣ አስገድዶ መድፈር ወዘተ.) የተለየና ዉስብስብ እንደሆነ ይገለጻል፡፡የዚህን ወንጀልን ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያደርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ ሙስና ወንጀልን ለመመርመር፣ለማጋለጥ፣ለመመርመር፣ለመክሰስና እጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ፡፡ስለሆነም ሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ የሚያደርጉት ነጥቦች እንደሚከተለዉ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 3.1 <u>የአፈጻጸሙ ስልት፣</u>

በዋናነት የተለመዱ ወይም ነባር የሚባሉት ወንጀሎች ከፍተኛ ጉጉት ወይም ጥላቻ ዉጤቶች ናቸዉ ማለት ይቻላል፣እነዚህ ወንጀሎች በባህሪያቸዉ ስሜታዊና አብዛኛዉን ጊዜ ሃይልን የሚጠቀሙ ሲሆን ተጠቂዎችም ባብዛኛዉ ግለሰቦች/ቡድኖች ናቸዉ፡፡ ብዙ ጊዜ ከጥላቻ፣ ከቂም በቀል፣ወዘተ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ደግሞ በቀላሉ ለማጋለጥና ለመመርመር ብሎም አጥፊዎችን ለማስቀጣት ቀላል ነዉ

በአንጻሩ የሙስና ወንጀል በሰሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጥርና በጥንቃቄ የሚፈጸም ነዉ፡፡በዚህም ምክንያት መፈጸሙን ለማወቅ የሚያስችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አይቻልም፡፡ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር ወይም በጥንቃቄ መፈጸሙ ብቻ ሳይሆን እጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል አሻራ የማጥፋት አቅም ስላለዉም ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል፡፡

### 3.2. <u>በሙስና የተሳተፈ ሁሉ በህግ አይን ወንጀለኛ መሆኑ.</u>

ሙስና ባብዛኛዉ ከአንድ በላይ ስዎችን ያካትታል፣ትስስሩ የሚፈጠረዉ በበላይና በበታች ሰራተኛ ወይም በዉሳኔ ሰጭና በዉሳኔ ተቀባይ መካከል ሊሆን ይችላል፡፡እነዚህ ደግሞ ሚስጥሩን የሚያዉቁ ብቸኛ ሰዎች በመሆናቸዉ ለጥቅማቸዉ ሲሉ ማስረጃ ሊሰጡ አይችሉም፤ ከዚህም በላይ ሁለቱም በህግ አይን ወንጀለኞች በመሆናቸዉ ሚስጥሩን

ይገፋበታል እንጅ ለማጋለጥ አይችሉም፣ለዚህ አባባል የጉቦ ወንጀልን በምሳሌነት መዉሰድ ይቻላል፣ ጉቦ ተቀባይ የተሰጠዉን የስራ ሀላፊነት ወይም የህዝብ አደራ ወደጎን በመተዉ ማድረግ የማይገባዉን በማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ባለድረግ ለጉቦ ሰጭ ጥቅም የሚያስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፣ ጉቦ ሰጭም በምትኩ ላገኘዉ ያልተገባ ጥቅም ገንዘብ ወይም የተለየ ጥቅም ለጉቦ ተቀባይ ይሰጣል፣ እነዚህ ሁለቱም በወንጀሉ ፍሬ ተጠቃሚዎች ከመሆናቸዉም በላይ በህግ አይን ወንጀለኞች ስለሚባሉ ሚስጥሩን ለመደበቅ ይገደዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ይህን ወንጀል ለማጋለጥ፣ ለመመርመር እና አጥፊዎችን ለማስቀጣት ይከብዳል፡፡

በአንጻሩ ነባር ወይም መደበኛ በሚባሉ ወንጀሎች አፈጻጸም ላይ እንደዚህ አይነት ትስስር ባለመኖሩ ወንጀሉ የተፈጸመበት ተጎጅ ጉዳት ያደረሰበትን ግለሰብ ለፍትህ አካላት ለመጠቆምና ለማጋለጥ በመቻሉ እንደዚህ አይነት ወንጀሎችን ለመመርመርና ለመክሰስ ልክ እንደሙስና ወንጀል አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡

## 3.3 <u>በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጠቂ አለመኖር፣</u>

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ሊኖር ግድ ይላል፣ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡

በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በወንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፣ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጅ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ስለሆነም በዚህ ምክንያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል::

## 3.4 <u>የወንጀል አፈጻጸም ተግባራቸዉ እንዳይታወቅ ማድረግ በሚችሉ መፈጸሙ፣</u>

በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ ሰዎች ህጉንና አሰራሩን የሚያዉቁ በመሆኑ አፈጻጸማቸዉ ከህግ ጋር ግጭት በማይፈጥርበት ሁኔታ ሽፋን በመስጸት ሊከናወን ይችላለል፣በረቀቀና በተቀነባበረ ዘዴ ወንጀሉን ስለሚፈጸሙ ወንጀሉን በቀላሉ ማጋለጥ የሚቻል አይሆንም፡፡

በተለይም ደግሞ በከፍተኛ የሙስና ወንጀል የሚሳተፉ ግለሰቦች የስልጣን አልያም የገንዘብ አቅሙ ስላላቸዉ ማስረጃ የማጥፋት፣ምስክሮችንና ሌሎች ሰዎችን የማስፈራራት በገንዘብ የመደለል ስራ በመስራት የፈጸሙት ወንጀል እንዳይጋለጥ ያደርጋሉ:: እነዚህ ግለሰቦች በመዘበሩት ገንዘብ የፍትህ አካላትን በመደለል ጉዳያቸዉ እንዳይጋለጥ ወይም እንዳይከሰሱና እንዳይቀጡ የማድረግ አቅምም አላቸዉ፡፡ቢከሰሱ እንኳ በመዘበሩት ገንዘብ ታዋቂ ጠበቆችን በመግዛት በፍርድ ቤት ላይ ጫና የማሳደርና ክረክሩን በበላይነት በመምራት ነጻ ለመዉጣት ይችላሉ፡፡ በህግ ፊት ተከሳሽ ደካማ ነዉ የሚለዉ አባባል ለሙስና ወንጀል ላይሰራ ይችላል፡፡

መደበኛ ወይም ነባር የሚባሉ ወንጀሎችን የሚፈጽሙት ባብዛኛዉ በመካከለኛ ወይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ደግሞ ወንጀሉ እንዳይጋለጥ ሊያደርጉ የሚችሉበት አቅም ላይኖራቸዉ ስለሚችል በቀላሉ ሊጋለጡና ሊቀጡ ይችላሉ፡፡ከአቅማቸዉ ማነስ የተነሳ ጠበቃ ለማቆምም ሆነ መከላከያ መስረጃ ለማሰባሰብ ስለሚቸገሩ በህግ ፊት ደካማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### 3.5. <u>ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ አለመኖር፣</u>

በራሽያኖች ዘንድ "የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" የሚል አባባል አለ፣ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፣ በአንጻሩ በአገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና

አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደር ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅግ ብዙ ነዉ፡፡ ይህ ሁኔታ ሙስና ወንጀል የተለየ ባህሪ እንዳለዉ ያሳያል፡፡

በአንጻሩ የተለመዱ ወይም ነባር የሚባሉት ወነጀሎች በቀጥታ በግለሰብ አልያም በቡድኖች ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ስለሚያደርሱ በወንጀል ድርጊቱ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ

ወይም ቡድን ድርጊቱን ለህግ በማቅረብ እና ማስረጃ በመስጠት ጉዳዩ ተዳፍኖ እንዳይቀር ያደርጋል፡፡

### 3.6. በህዝቡ ዘንድ እንደነዉር አለመታየቱ፣

ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለዉ አባባል በአገራችን የተለመደ ነዉ፤ይህ አባባል ሙሰኞች በድርጊታቸዉ እንዲበረታቱ በአንጻሩ ሙሰኞችን ለማጋለጥ የሚሞክሩ ካሉ ምቀኛ፣ጸረ-ምቾት የሚል የዉግዘት ካባ እንዲላበሱ ያደርጋል፡፡ሙሰኞችን የሚያበረታታ በአንጻሩ ንጹህንን የሚኮንን አመለካከት ባለበት የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ለማስቀጣት አይቻልም፤በዚህ ምክንያት የሙስና ወንጀል ከነባር ወንጀለች እንዲለይ ያደርገዋል፡፡

ህብረተሰቡ እንደ ግድያ፣ እገድዶ መድፈር ወዘተ መሳሰሉ ወንጀሎች መፈጸማቸዉን ሲሰማ ሲዘገንኑና ሲያወግዝ ይስተዋላል፡፡ ወንጀለኞቹ በአፋጣን ህግ ፊት ቀርበዉ እንዲቀጡ አስፈላጊዉን ድጋፍ ሊያደርግም ይችለል፡፡እንዲህ አይነት ድጋፍ ባለበት ደግሞ የተፈጸመዉን ወንጀል በቀላሉ ማዉጣትና አጥፊዎቹንም ለማስቀጣት ቀላል ይሆናል፡፡

### 3.7 ወሰን ተሸጋሪነት፣

ሰዎች የሙስና ወንጀል የሚፈጽሙበት ዋናኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብረተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች/ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል::

በአንጻሩ መደበኛ ወይም ነባር የሚባሉ ወንጀሎችን የሚፈጽሙ ግለሰቦች ዋናዉ አላማቸዉ ብቀላ ወይም ሊሆን ስለሚችል ወንጀሉን ለመፈጸም በአገር ዉስጥ ያለ

ግለሰብን ቤባባሪነት ሊጠቀሙ ከሚችሉ በስተቀር እንደሙስና ወንጀል ድንበር ተሸጋሪ ረዳቶች ሊያደራጁ አይችሉም፡፡

### 3.8. <u>የዘመድ ወይም የጓደኛ ድርጅትን እንደሽፋን መጠቀም፣</u>

ሙሰኞች በሙስና ተዘፍቀዉ ከፍተኛ ሃብት ቢያካብቱም በኑሯቸዉ/በገቢያቸዉ ምንም አይነት ለዉጥ ላይታይባቸዉ ይችላል፣በተለይም እንጂ በቤተሰቦቻቸዉ/በጓደኞቸዉ ስም ንግድ ሊያካሂዱ እንዲሁም የበቤተሰቦቻቸዉ/በጓደኞቸዉን አካዉንት በሙስና ያገኙትን ገንዘብ በስዉር ለማጠራቀም ሊገለገሉበት ይችላሉ፣በዚህ ምክንያት ወንጀሉን ለማጋለጥና አጥፊዎችን ለመቅጣት ይከብዳል፡፡

## 4. <u>ሙስናን ከማጋለጥ፣መመርመርና መክሰስ አኳያ በአገራችን የተወሰዱ እርምጃዎች፣</u>

አገራችን አለም አቀፍና አህጉራዊ የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኖችን የተቀበለች በመሆኗ በርካታ እርምጃዎች ከሞላ ጎደል አድርጋለች፡፡ከወሰደቻቸዉ እርምጃዎች መካከል የሙስና ወንጀሎችን በግልፅ መደንገግ አንዱና ዋነኛዉ ነዉ፡፡

በአገራችንም እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ የሙስና ወንጀልን ሊተረጉም የሚችል ግልፅ ድንጋጌ ባይኖርም የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉ እንደጉቦና በስልጣን አለአግባብ መገልገል የመሳሳሉት በ1949 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ዉስጥ ተደንግገዉ ነበር፡፡ ይህንና እነዚህ ድንጋጌዎች የተሟሉ ካለመሆናቸዉም በላይ የሚጥሉት ቅጣት እጥፊዎችን ሊያርም የሚችል አልነበረም፣ በደርግ ስርዐትም ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ (አዋጅ ቁጥር 8/67 እና 214/74) ወጥቶ የነበረ ቢሆንም ልክ እንደ 1949 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የሙስና መገለጫ የሆኑ ጥቂት ወንጀሎችን ከመደንገግ ባለፈ የተሟላ አልነበረም፡፡

በ1949 የወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግም ሆነ በደርግ ስርዐት የወጣዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የሙስና ወንጀሎች የትኞቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ በግልጽ ለይተዉ ያላስቀመጡ እና የተሟሉም ባለመሆናቸዉ እንዲሁም ይህን ሊያሳይ የሚችል ሌላ ህግ

ባለመኖሩ የፌደራል የስነምግባርና የጸረሙስና ኮሚሽን መቋቋምን ተከትሎ ሙስና ወንጀሎችን ቢያንስ በትርጉም ደረጃ ሊሰበስብ የሚችል ልዩ የስነስርዐትና የማስረጃ ህግ ሊወጣ ችሎ ነበር፤(አዋጅ ቁጥር 236/93 )፡፡ ይህ አዋጅ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሙስና ወንጀል ትርጓሜ እንዲሰጠዉና በስራ ላይ በነበሩት የወንጀል ህጎቻችን ዉስጥ ከሚገኙ ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ለማስቀመጥ የቻለ የመጀመሪያዉ ህግ ሊሆን ችሏል::

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ስለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜም የሚከተለዉን ይመስላል ፣

‹

*"የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመተጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ለቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን እና ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል"*

ይህ ትርጓሜ ጉቦ መስጠትና ማቀባበልን እንዲሁም አዳዲስ የሚከሰቱ እንደ መኒ ላዉደሪንግ የመሳሳሉትን ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ "....የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል" ተብሎ የተቀመጠዉ አረፍተ ነገር በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

አሁን ደግሞ ከግንቦት 1 ቀን 1997 ስራ ላይ እንዲዉል የተደረገ አዲስ የወንጀል ህግ በአገራችን ወጥቷል፤በዚህ የወንጀል ህግ ዉስጥ ስለሙስና ወንጀል ቀጥተኛ ትርጉም ተቀምጦ ባናገኝም ወንጀሉ በመንግስት ሰራተኛ ወይም በማንኛዉም ሰዉ ሊፈጸም የሚችል መሆኑን (በአንቀጽ 404/3) እና ከወንጀል ህጉ ክፍሎች ዉስጥ የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉት የትኞቹ ድንጋጌዎች እንደሆኑ በማያሻማ መንገድ

ተቀምጠዋል፤(አንቀጽ 404/4)፡፡ በዚህ ህግ አወቃቀር መሰረት የሙስና ወንጀል ተብለዉ የተለዩት 23 አንቀጾች ብቻ ናቸዉ፡፡ እነዚህ የሙስና ወንጀሎች በመንግስት ሰራተኛ (አንቀጽ 407 እስከ 419፣676/1 እና 696/ሀ)፣ከመንግስት ስራ ጋር በተያያዘ በሌሎች ሰዎች(አንቀጽ 427 እስከ 431) እንዲሁም በማናቸዉም ሰዉ (አንቀጽ **379?**፣468 እና 684) ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ከወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በወንጀል ህግ በመንግስት ስራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚለው ምእራፍ በአንቀጽ 404 በተደነገገው መርህ ንኡስ አንቀጽ (3) የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

«ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በተሰጠው ሀላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ፣ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ ወይም

ማንኛውም ሰው ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት ቃል የገባ ወይም ያቀረበ ወይም ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ ወይም

በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት ስራ የማይገባ ጥቅምን ማንኛውም ሰው የሰጠ ወይም ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ፣

በዚህ ርእስ የተመለከቱትን የሙስና ወንጀሎች አድርጓል ተብሎ ከዚህ በታች በተጻፉት ድንጋጌዎች የተመለከተው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የሙስና ወንጀል በመንግስት ሰራተኛ እና በማንኛውም ሰው ሊፈጸም ይችላል፡፡ ይሁንና በመንግስት ሰራተኛ የሚፈጸመው የሙስና ወንጀልና በሌላ በማንኛውም ሰው ከሚፈጸመው የሙስና ወንጀል ይለያያል፡፡

የመንግስት ሰራተኛ ማንነው?

**<u>የመንግስት ሰራተኛ ማለት ምን ማለት ነው?</u>**

የወንጀል ህግ አንቀጽ 402(1) የመንግስት ሰራተኛን፣

- በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት
- ተቀጥሮ፣ ተሹሞ፣ ተመድቦ ወይም በህዝብ ተመርጦ

በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት

ስራን የሚያከናውን ሰው ነው በማለት ይተረጉማል፡፡

በዚህ ትርጉም መሰረት የመንግስት ሰራተኛ ለመባል በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ውስጥ መስራት ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በወንጀል ህግ አንቀጽ 402(2) እንደተመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር የፌዴራል ወይም የክልል መስሪያ ቤት ነው፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤት ተብሎ ለመለየት ዋናው መመዘኛ በመንግስት በጀት የሚተዳደር ማለት ነው፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤት ለመባል ሁሉም በጀት በመንግስት መሸፈን የለበትም፡፡ በመንግስት በጀት የሚሸፈነው ወጪ ከፊል ቢሆንም የመንግስት መስሪያ ቤት መባሉን አያስቀረውም፡፡ ስለሆነም የመንግስት በጀት (በሙሉም ሆነ በከፊል) እየተመደበለት የሚሰራ መስሪያ ቤት ማለትም ከተወካዮች ምክር ቤት ጀምሮ ያሉት እንደመንግስት መስሪያ ቤት የሚቆጠሩ ናቸው ማለት ነው፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅት ማለት ደግሞ በወንጀል ህግ አንቀጽ 402(3) እንደተመለከተው «የመንግስት የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌዴራል ወይም የክልል የልማት ድርጅት ወይም አክስዮን ማህበር ነው፡፡»

በዚህ ትርጉም መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅት ለማለት መስፈርቱ መንግስት በድርጅቱ የባለቤትነት ድርሻ(ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል) ያለው መሆኑ ነው፡፡

ስለሆነም የመንግስት ሰራተኛ ማለት በእነዚህ ተቋማቶች (የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት) ተመርጦ የሚሰራ (የተወካዮች ምክር ቤት አባላትን)፣ ተሻሚዎችን (ሚኒስትሮችን፣ ስራ አስኪያጆችን ወዘተ) ተቀጣሪዎችን (የሂሳብ ሰራተኛ፣የጥበቃ ሰራተኞችን ወዘተ) ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

ይሁንና እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ወይም ማናቸውም ሰዎች ምን ሲሰሩ ነው የሙስና ወንጀል ፈጸሙ የሚባለው?

በወንጀል ህጉ አንቀጽ 404 እንደተመለከተው
የመንግስት ሰራተኛ፣

የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ፣

1. በተሰጠው ሀላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዲያደርግ

    ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ እንደሆነ

    ወይም

2. በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሰጠውን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ

    ወይም

3. በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት ስራ የማይገባ ጥቅምን የተቀበለ እንደሆነ

በሙስና ወንጀል እንደሚጠየቅ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የመንግስት ሰራተኛ በሶስት መንገዶች የሙስና ወንጀልን ሊፈጽም ይችላል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በታች ተራ በተራ እንመልከታቸው፡፡

1. የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በተሰጠው ሀላፊነት ወይም ተግባር ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ወይም ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ ይላል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ከሀላፊነቱ ጋር በተያያዘ ማድረግ የማይገባው ተግባር አለ፡፡ ለምሳሌ መስፈርቱን ላላሟላ ሰው ፈቃድ መስጠት ማድረግ የማይገባው ነው፡፡ የማይገባውን ማድረግ በራሱ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ከላይ በትርጉሙ እንደተቀመጠው የሙስና ወንጀል የሚሆነው በተጨማሪ ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ እንደሆነ ነው፡፡ ስለሆነም የመንግስት ሰራተኛ ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ጥቅም ተቀብሎ ወይም ጠይቆ ከሆነ በሙስና ወንጀል ሊጠየቅ ይችላል ማለት ነው፡፡
2. ይሁንና ከሌላ ሰው ወይም አገልግሎት ፈላጊ ላይ ጥቅም መጠየቅ ወይም መቀበል አንደኛው ሙስና መፈጸሚያ መንገድ ነው እንጂ ብቸኛ መንገድ አይደለም፡፡ ሁለተኛው መንገድ ከላይ እንደተመለከተው ጥቅም ሳይጠይቅም ሆነ ሳይቀበል ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ስልጣኑን ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነም የሙስና ወንጀል ይሆናል፡፡ ስለሆነም በእጁ የገባውን ስልጣን ወይም ንብረት ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ወገን ጥቅም እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ስልጣኑን በመጠቀም የሀሰት ሰነድ በማዘጋጀት ከመንግስት ካዝና ገንዘብ ለራሱ ቢወስድና ለግል ጥቅሙ ቢያውል ማለት ነው፡፡
3. ሶስተኛው መንገድ በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት ስራ የማይገባ ጥቅምን የተቀበለ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የመንግስት ሰራተኛው የሚጥሰው ህግ የለም፡፡ የፈጸመው ተግባር ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ነው፡፡ ለምሳሌ ተገቢውን ታክስ ተገልጋይ እንዲከፍል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይሁንና ለዚህ አገልግሎቱ ከተገልጋይ ጥቅም ሊጠይቅና ሊወስድ ይችላል፡፡ ይሁንና በአግባቡ ለተሰራ ስራም ቢሆን የመንግስት ሰራተኛ በህግ ከተፈቀደለትና በመንግስት ከሚከፈለው ክፍያ ሌላ ጥቅም መቀበል የለበትም፡፡ ይህንን ያደረገ እንደሆነ የሙስና ወንጀል ይሆናል ማለት ነው፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ለሌላ ሰው ጥቅም የሰራ እንደሆነ የሚል ሀረግ አለ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ የመንግስት ሰራተኛው በሚፈጽመው ህገወጥ ድርጊት የጥቅሙ ተቀባይ ልጁ ወይም ሌላ ዘመዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ልጁ ነጻ ትምህርት እድል እንዲያገኝ ተደርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ የነጻ ህክምና አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ በተቀመጠው መርህ ውስጥ ሌላው የምናገኘው ሀረግ «የማይገባ ጥቅም ለማግኘት» የሚለው ነው፡፡

የማይገባ ጥቅም ማለት ምንድነው?

- የወንጀል ህግ አንቀጽ 402(5) የማይገባ ጥቅምን
- ተገቢ ያልሆነ ጥቅም

አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም

በማለት ይተረጉመዋል፡፡

ይህ ምን ማለት ነው?

በወንጀል ህጉ ውስጥ ከዚህ በላይ ማብራሪያ አናገኝም፡፡ ይሁንና ተገቢ ያልሆነ ጥቅም የሚለውን ተገቢ ከሆነው ጥቅም ጋር በማነጻጸር ለመተርጎም እንሞክር፡፡ ለመንግስት ሰራተኛ ደመወዙና ከስራው ጋር በተያያዘ በህግና በመመሪያ ተደግፎ የሚያገኘው ጥቅም ተገቢ የሆነ ጥቅም ነው፡፡ ምክንያቱም ለሚሰራው የሚከፈለው ነውና፡፡ ይሁንና ከደመወዙ በተጨማሪ የመንግስት ስራ በመስራቱ ከተገልጋይ ወይም በሌላ መልኩ የሚወስደው ጥቅም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ሊባል ይችላል፡፡

አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅምስ ምንድነው? የተገኘው ጥቅም ከስራው ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና የተገኘበት መንገድ አግባብ ያልሆነ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ለምሳሌ ደብተር በገበያ የሚሸጥበት ዋጋ የታወቀ ነው፡፡ ይሁንና በርካታ ደብተር ለመግዛት ጨረታ አውጥቶ ማወዳደር እየተቻለ ከአንድ አቅራቢ ያለጨረታ እንዲገዛ ማድረግ አቅራቢው ያለውድድር ከፍተኛ መጠን ያለው ግዢ በማድረግ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን የተገዛበት ዋጋ በገበያ ዋጋ ቢሆንም፣ያለጨረታ ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ስለሆነ ድርጊቱ የሙስና ወንጀል ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሙስና ወንጀል ሊገኝ የሚችል የማይገባ ጥቅም ምንድነው? ብዙውን ጊዜ ሁላችንም የምንረዳው ገንዘብና ንብረትን ነው፡፡ ይሁንና በሙስና ወንጀል የሚገኙ ጥቅሞችን አይነት ዘርዝሮ መጨረስ ያስቸግራል፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 402(4) ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ጥቅም ለሚለው ትርጓሜ አስቀምጧል፡፡

ጥቅም ማለት፣

1. በገንዘብ ወይም በማናቸውም ዋጋ ባለው መያዣ ወይም በሌላ ንብረት ወይም በንብረት ላይ ባለጥቅም (መብት) የሚተመን ማናቸውም ስጦታ፣ ብድር፣ ክፍያ፣ ወሮታ(ሽልማት) ወይም ኮሚሽን፣
2. ማናቸውም ሹመት፣ ቅጥር ወይም ውል፣
3. ብድርን፣ ግዴታን ወይም ማናቸውንም እዳ በሙሉም ሆነ በከፊል ማስቀረት፣ ማወራረድ ወይም ከአነዚህ ነገሮች ነጻ ማድረግ
4. ከተመሰረተ ወይም ካልተመሰረተ የአስተዳደር ወይም የፍትሀብሄር ወይም የወንጀል ክስ ወይም ካስከተለው ወይም ከሚያስከትለው ማናቸውም ቅጣት ወይም የችሎታ ማጣት በማዳን ወይም ይህን በመሰለ ዘዴ የሚደረግ አገልግሎት ወይም ውለታ
5. ማናቸውንም መብት፣ ተግባር ወይም ግዴታ መፈጸም ወይም ከመፈጸም መታቀብ

ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ በገንዘብ የማይተመን ማናቸውም ሌላ ጥቅም ወይም አገልግሎት

እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

## <u>ማንኛውም ሰው የሙስና ወንጀል ፈጸመ የሚባለው ምን ሲያደርግ ነው?</u>

<u>***የመወያያ ጥያቄ፣***</u>

አቶ አበበ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ዉስጥ የአንድ ተቋም ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ኮሌጅ አብሮት የተማረ አንድ ጓደኛዉ ከእንግሊዝ ሃገር በመምጣት በድንገት ይደዉልለትና ይገናኛሉ፣ብዙ ከተጨዋወጡ ቦሃላም ከዉጭ የመጣዉ ጓደኛ አበበን ውጭ አገር ወስዶ ለማዝናናት እንደመጣ ይገልጽለትና የአየር ትኬት ቆርጦ ይሰጠዋል አበበም

እንግሊዝ አገር ሄዶ እጅግ ዉድ የተባለ ሆቴል አርፎ ለ15 ቀን ከተዝናና ለኪሱ ገንዘብ ከሰጠዉ ቦኋላ ወደአገሩ ይመለሳል አበበ ይህን ግብዣ በመቀበሉ ጥቆማ ቢቀርብበት የሙስና ወንጀል ፈፀመ ማለት እንችላለን?ግብዣ ያደረገለት ሰዉ እዚሁ አገር ነዋሪ ቢሆንስ ለዉጥ ያመጣል?

ማንኛውም ሰው፣

1. ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማሰብ ለመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለመስጠት

- ቃል የገባ ወይም
- ያቀረበ ወይም
- ለማቅረብ የተስማማ እንደሆነ

ወይም ፤

2. በአግባቡ ለተፈጸመ ወይም በአግባቡ ወደፊት ለሚፈጸም የመንግስት ስራ የማይገባ ጥቅምን የሰጠ እንደሆነ

የሙስና ወንጀል ፈጸመ ተብሎ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ሌላ ሰው እንዲጎዳ ማለት ምን ማለት ነው? ለምሳሌ በንግድ ተወዳዳሪው የሆነው ሰው ድርጅት እንዲዘጋ፣ ፈቃዱ እንዳይታደስለት ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም ለመንግስት ሰራተኛ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው ሙስና በመንግስት ሰራተኛም ሆነ በሌላ በማንኛውም ሰው ሊፈጸም እንደሚችል ነው፡፡ ይሁንና ሙስና የሚያሰኘው ተግባሩ በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ስራ ላይ መፈጸሙ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የግል ባንክ ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከደንበኛ «ጉቦ» በመቀበል ሊሰጥ የማይገባ ብድር እንዲፈቀድ ቢያደርግ፣ በወንጀል ባህርዩ በመንግስት ባንክ ከሚፈጸም ተመሳሳይ ተግባር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይሁንና በመንግስት ባንክ የተፈጸመው ተግባር ሙስና ሲባል በግል ባንኩ የተሰራው ተግባር ግን ሙስና አይባልም፡፡ ይህ ማለት ግን በግል ባንኩ የተፈጸመው ተግባር አያስጠይቅም፣ ወንጀል አይደለም ማለት አይደለም፡፡ የሙስና ወንጀል አይደለም ማለት ብቻ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የማይገባውን ለማግኘት በግል ባንክ ሰራተኛ ለሆነ ሰው የማይገባ ጥቅም የሰጠ አንድ ተበዳሪ የፈጸመው ድርጊት ሙስና አይባልም፡፡ ይሁንና ተበዳሪው የማይገባ ጥቅም የሰጠው የመንግስት ባንክ ሰራተኛው የማይገባ ብድር እንዲሰጠው ከሆነ ድርጊቱ ሙስና ይሆናል ማለት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## 5.የሙስና ወንጀል ምርመራንና የክስ ስርአትን ለመደገፍ የተደነገጉ መሰረተዊ የስነስርአትና የማስረጃ ድንጋጌዎች

የሙስና ወንጀልን የመመርመር፣ የመክሰስ እንዲሁም የክስ ሂደቱ እንደማንኛውም ወንጀል በወንጀል ስነስርአት ሕግ የሚመራ ቢሆንም፣ ከሙስና ወንጀል ልዩ ባህርይ አንጻር የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ሕግ ወጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው፡፡

### 5.1. የሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን፣

ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 334/93 የአዋጁን የአፈጻጸም ወሰን በተመለከተ በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ አልነበረም፡፡ ይሁንና በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ሕግ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 3 በፌዴራልና በክልል ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡

የሕጉ ተፈጻሚነትም በሙስና ወንጀሎች ላይ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ ሕጉ ትርጉም የሰጠው ሲሆን፣ ይህም በወንጀል ሕጉ ላይ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ይሁንና ለምሳሌ ያህል በተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ፣የኮሚሽኑን ስልጣን ሲገልጽ በወንጀል ህግና በሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱ የሙስና ወንጀሎችን

ስለሚል፣ በሌሎች ሕጎች የተመለከቱትን የሙስና ወንጀሎች በሚመለከት 434/97 ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል ወይ?[1] የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ፡

<u>**መወያያ ጥያቄ**</u>

አንድ ሰው የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ያመለክታል፡፡ ክሱን ያዳመጠው መርማሪ፣ ይህ የፖሊስ ስልጣን አይደለም፣ የሙስና ወንጀል ስለሆነ ጸረ ሙስና ኮሚሽን በመሄድ አመልክቱ በማለት ይመልሳቸዋል፡፡ በፖሊስ ጣቢያው የተሰጠው ምላሽ ትክክለኛና በሕግ የተደገፈ ስለመሆኑ ተወያዩበት፣

1. <u>**አግባብ ያለው አካል**</u>

የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ወይም ለመክሰስ የሚችለው ማን ነው? የሙስና ወንጀልን በሚመለከት አከራክሮ ውሳኔ ለመስጠት የሚችለው ማን ነው? በዚህ ክፍል ለአነዚህ ጥያቄዎች በህጉ የተቀመጠውን ምላሽ እንመለከታለን፡፡

በጸረ ሙስና የስነስርአትና የማስረጃ ህግ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 3 «አግባብ ያለው አካል» ማለት የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና /ወይም ለመክሰስ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው በማለት ይተረጉማል፡፡

<u>**ሙስናን ለመመርመርና ለመክሰስ አግባብ ያለው አካል ማንነው?**</u>

በፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 7(4) እንደተመለከተው በመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ወይም ፌዴራል መንግስቱ ለክልሎች ከሚሰጠው ድጎማ ጋር በተያያዘ በክልል መስሪያ ቤቶች በወንጀል ህግና በሌሎች ህጎች የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግስት ሰራተኞች ወይም ባለስልጣኖች ወይም በሌሎች ሰዎች ስለመፈጸማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ

---

[1] የክልል ኮሚሽን ማቋቋሚያ ህጎችም ተመሳሳይ አቀራረጽ እንዳላቸው ይገመታል፡፡ ለምሳሌ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ ተመሳሳይ ድንጋጌ አለው፡፡

ጥርጣሬ ሲኖረው ኮሚሽኑ የመመርመር ወይም የመክሰስ ወይም እንዲመረመር ወይም እንዲከሰስ የማድረግ ስልጣን እንደአለው ያመለክታል፡፡[2]

በዚሁ በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ በአንቀጽ 8(2) ደግሞ ማንኛውም ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን የተሰጠው አካል ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ምርመራ መጀመርና ለኮሚሽኑ ማሳወቅ እንደሚኖርበት ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም በአጭሩ ከጸረ ሙስና ኮሚሽን በተጨማሪ ማንኛውም ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን ያለው የፌዴራልም ሆነ የክልል የምርመራ አካል የሙስና ወንጀልን መመርመር ይችላል ማለት ነው፡፡

1. በአዋጁ አንቀጽ 8 እንደተመለከተው ሌሎች የምርመራ አካላት የሙስና ወንጀልን መመርመርን በተመለከተ ያላቸው ስልጣን በሁለት መልኩ ሊተይ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ለፌዴራልም ሆነ ለክልል ምርመራ አካላት የሙስና ወንጀልን እንዲመረምሩ ሙሉ ውክልና የሰጠ ከሆነ፣ የምርመራ አካላቱ እንደማንኛውም የወንጀል ጉዳይ ምርመራውን በማድረግ ምርመራውን ሲያጠናቅቁ በጉዳዩ ላይ ለመወሰን ስልጣን ላለው አቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን ይልካሉ፡፡
3. በሌላ በኩል ኮሚሽኑ ውክልና ያልሰጣቸው የፌዴራልም ሆነ የክልል አካላት የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ መረጃ ከደረሳቸው ወይም በቂ ጥርጣሬ ካላቸው፣ ምርመራውን የመጀመር ግዴታ አለባቸው፡፡ ይሁንና ምርመራ ስለመጀመራቸው ለኮሚሽኑ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ኮሚሽኑ ምርመራ የተጀመረበትን ጉዳይ ሲያውቅ፣ ጉዳዩ እራሱ ወስዶ ሊመረምረው ወይም ምርመራውን እንዲቀጥሉበት ሊወስን ይችላል፡፡ ይሁንና የምርመራ አካሉ የሙስና ወንጀል ምርመራ መጀመሩን ለኮሚሽኑ ሲያሳውቅ የጀመረውን ምርመራ ይቀጥላል፡፡ የምርመራ አካሉ የጀመረውን ምርመራ የሚያቆመው፣ ኮሚሽኑ እኔ እራሴ እመረምረዋለሁ፣ ወይም ሌላ አካል እንዲመረምር ውክልና ሰጥቻለሁና የምርመራ መዝገቡን አስረክብ ካለው ብቻ ነው ምርመራውን የሚያቆመው፡፡ የምርመራ አካሉ

[2] በየክልሉ የኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጆች የተሰጡት ስልጣኖች ሊለያዩ ስለሚችሉ እነዚህን ህጎች ባካተተ መልኩ ስልጣኞች ይህንን ክፍል ይመልከቱ

ምርመራ መጀመሩን ለኮሚሽኑ አሳውቆ፣ ከኮሚሽኑ ምላሽ ካልመጣለት፣ የመጀመረውን ምርመራ በማጠናቀቅ ስልጣን ላለው አቃቤ ህግ ይልካል፡፡

የሙስና ወንጀልን የመክሰስ ስልጣንን በሚመለከት የኮሚሽኑ ስልጣን እንደሆነ ከዚህ በላይ በተመለከተው ድንጋጌ የተመለከተ ሲሆን፣ ይሁንና ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ለሌሎች አካላት ሊሰጥ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 9 ተመልክቷል፡፡
በፌዴራል መንግስቱ ለክልሎች ከሚሰጥ ድጎማ ጋር በተያያዘ የክልል ጸረ ሙስና ተቋም ወይም በክልሉ ሙስና ወንጀልን ለመክሰስ ስልጣን ያለው አካል ክስ መመስረት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሁንና ኮሚሽኑ አስፈላጊ መስሎ ከታየው በቀጥታ በክሱ ውስጥ ሊገባ እንደሚችልም በአንቀጽ 9(2) ተደንግጓል፡፡

**2. <u>የዳኝነት ስልጣን</u>**

በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7 መሰረት የሙስና ወንጀልን የሚመለከቱ ማንኛውንም ጉዳዮች በሚመለከት የመወሰን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመንግስት ባለስልጣኖችን በተመለከተ በክልል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን በፌዴራል የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡
    - የመንግስት ባለስልጣን የሚባሉት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ከሚኒስትር በላይ የሆኑ ባለስልጣኖች፣ የቢሮ ሀላፊዎችና ከቢሮ ሀላፊዎች በላይ የሆኑ ባለስልጣኖች፣ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትረ ዴኤተዎችና ምክትል ሚኒስትሮች የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን ያካትታል፡፡
2. የመንግስት ባለስልጣኖች ከሆኑት ውጭ ያሉትን የሙስና ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት በክልል የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በፌዴራል የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡
3. የዉጭ ሃገር አምባሳደሮችና ቆንፅላዎች እንዲሁም የአለም አቀፍ ድርጅቶችና የዉጭ መንግስታት ወኪሎች ያሉበትን የሙስና ወንጀል መርምሮ የመወሰን ስልጣኑ የፍደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡(አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8)

የፍርድ ቤቶችን ስልጣን በተመለከተ ሕጉ በፌዴራልም ሆነ በክልል ለፍርድ ቤቶች ተሰጥተው የነበሩ አዋጆችን የሚያሻሽል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተለይ በክልል ስልጣኑ የተሰጠው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የሚታዩ

የብርበራ፣ የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይም ይህው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እንዲመለከተው በመደረጉ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እነዚህን ጉዳዮች እንደሚያስተናግዱ ይታወቃል፡፡ በአዲስ አበባ ደረጃም ቢሆን የጊዜ ቀጠሮ የመሳሰሉት ጉዳዮች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሚስተናገዱበት ጊዜ ጥቂት አይደለም፡፡ ለእነዚህ ጉዳዮች መከሰት አዋጁ በግልጽ ያላስቀመጠው መሆኑ የፈጠረው ችግር ነው፡፡ ከወንጀል ሕግና ሕገመንግስቱ የተከሳሾችን በተፋጠነ መልኩ ፍትህ ከማግኘት አንጻር በፍርድ ቤቶች እየተደረገ ያለውን ነገር መመልከት ያስፈልጋል፡፡
ሌላው አስቸጋሪው ነገር በተለይ በክልል ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ያላቸው የፌዴራል መስሪያ ቤቶችን በሚመለከት፣ ለሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች በክልል የሚገኙ የፌዴራል ፍርድ ቤት ውክልና ያላቸው ፍርድ ቤቶች ለማየት ይችላሉ፡፡ ይሁንና ውክልና በሌላቸው ፍርድ ቤቶች ለምሳሌ በደቡብ፣ ጋምቤላ ወዘተ የሙስና ወንጀል ተፈጽሞ ቢገኝ ክሱ የት ይቀርባል የሚለውም ከህጉ አንጻር ስንመለከተው አስቸጋሪ ነው፡፡

በተለይም በክልል የብርበራም፣ የመያዝም የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይም ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሰጠቱ ተግባራዊ ለማድረግ የማይቻል በመሆኑ በተግባር ሕጉ እየተተረጎመ አይደለም፡፡
ችግሮቹ በይበልጥ ጎልተዉ የሚታዩት ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን የተሰጠዉ ፍርድ ቤት ከሚያስችልበት የቦታ ርቀት፣በጥቆማ ደረጃ የሙስና ወንጀል መሆን አለመሆኑን ከመለየት ጋር እንዲሁም ስልጣን በሌለዉ ፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዛት ህጋዊ ዉጤት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ እነዚህን ነጥቦች በመዳሰስ ችግሮቹን ለማሳየት ይሞከራል፡፡

## ስልጣን የተሰጠዉ ፍርድ ቤት ከሚያስችልበት የቦታ ርቀት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች፣

ለማጓጓዝ የሚወስደዉን ጊዜ ሳይጨምር ማንኛዉም ተጠርጣሪ በተያዘ በ48 ሰዐታት ዉስጥ በአቅራቢያዉ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት(በወንጀለኛ መቅጫ ስነስረዐት ህጉ አገላለፅ በጣም አቅራቢያዉ ወደሆነዉ ፍርድ ቤት) ሊቀርብ እንደሚገባ በኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 19/3 እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነስረዐት ህግ ቁጥር 29 በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ የተጠርጣሪን በአፋጣኝ በፍርድ ቤት የመነብኘት መብት

(የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት) ማረጋገጥ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ህብረተሰቡ የተጠርጣሪን የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት እንዲጠበቅ የመፈለጉን ያህል የተፈጸመዉ ወንጀል በምርመራ ተጋልጦ አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡም ይፈልጋል፡፡ ይህን የህዝብ ፍላጎት ከማረጋገጥ አኳያ ፍርድ ቤቶች ሁለቱንም ፍላጎቶች በሚያማክል (ባላንስ ባደረገ) መልኩ መስራት እንዳለባቸዉ አያከራክርም፡፡ ስለሆነም አንድ ተጠርጣሪ ፍርድ ቤት እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ በዋስ ሊለቀዉ አልያም ለመርማሪዉ የምርመራ ቀነቀጠሮ በመፍቀድ በእስር እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል(የወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 59/2/3)፡ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዉ በእስር ሆኖ ምርመራ እንዲጣራ ሲወስን ለዚህ ስራ የሚሰጠዉ ቀነቀጠሮ በአንድ በኩል የተጠርጣሪን የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት በሌላ በኩል ደግሞ መርማሪዉ የተፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት በአግባቡ አጣርቶ አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ሀላፊነቱን እንዲወጣ የሚያስችል መሆን ይገባዋል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ የዳኞች እዉቀት እጅግ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠዉ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተቀመጠዉ የሙስና ወንጀል ክሶች እና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ የሚታዩት በፌደራል ጠቅላይ ወይም ከፍተኛ ወይም በክልሉ ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፣በዚህ መሰረት ለህዝቡ ቅርብ የሆኑ የመጀመሪያ(ወረዳ) ፍርድ ቤቶች ስልጣን የላቸዉም ማለት ነዉ፡፡ ስልጣኑ የተሰጣቸዉ ፍርድ ቤቶች ደግሞ በማዕከልና በዞን ከተማ ደረጃ ላይ ያሉ በመሆናቸዉ ወንጀሉ ከተፈጸመበት ቦታ ወደነዚሁ ፍርድ ቤቶች እየተመላለሱ ጊዜ ቀጠሮ መጠየቅ፣የብርበራ ወይም የመያዣ ወይም የንብረት ዕግድ ትዕዛዝ ማግኘት በተግባር ሲታይ ከላይ በተጠቀሱተ የህዝብ ፍላጎት ላይ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡
ይህንን አባባል በግለጽ ለማሳየት የሚከተሉትን ማሳያዎች እናያለን፤

<u>ማሳያ አንድ፦</u>

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጂንካ ቅርንጫፍ ሰራተኛ የነበረ አንድ ግለሰብ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ ተይዟል እንበል፣ተከሳሽ የፌደራል መስሪያ ቤት ሰራተኛ በመሆኑ ከዚሁ ወንጀል ጋር ተያይዞ በዚሁ ተጠርጣሪ ላይ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ስልጣኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ከኦሮሚያ፣ትግራይ ፣አማራና ሀረሪ ክልሎች ዉጭ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲደራጅ በመወሰኑ ከነዚህ ዉጭ ያሉ

ፍርድ ቤቶች የፌደራል ፍርድ ቤትን ስራ በዉክልና ሊያዩ አይችሉም ።(የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/97 አንቀጽ 2)፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ በአዋጁ መሰረት በተባሉት ክልሎች በተግባር የተደራጀ ሳይሆን ተዘዋዋሪ የሚሰራ በመሆኑ መርማሪዉ የምርመራ ማጣሪያ ቀነቀጠሮ ቢፈልግ ከላይ የተጠቀሰዉን ተጠርጣሪ አዲስ አበባ ይዞ ሊቀርብ ግድ ይሆናል።ፍርድ ቤቱ የምርመራ ማጣሪያ ቀነቀጠሮ ቢሰጥም ማስረጃዉ ያለዉ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ (ጅንካ) በመሆኑ መርማሪዉ ከጂንካ አዲስ አበባ እየተመላለሰ ሊያጣራ ቢሞክር ከሚኖረዉ የሪሶርስ ዉስንነት፣ ከቦታዉ መራቅ ወዘተ. አንጻር እንደታሰበዉ ሊያደርግ አይችልም።እንዲያዉም የተሰጠዉ የምርመራ ማጣሪያ የቀነ ቀጠሮ ጊዜ በመንገድ ምልልስ ስለሚጠፋ ምርመራዉን የተጠርጣሪዉን የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት ሳይነካ ሊፈጸም እንደማይችል ግልጽ ይሆናል፣ፍርድ ቤቱ ይህን የተጠርጣሪዉን መብት ለማስከበር ቢሞክር ደግሞ መርማሪዉ በቂ ጊዜ አግኝቶ ጉዳዩን በአግባቡ እንዳያጣራና ወንጀለኛዉ እንዳይጠየቅ ስለሚያደርግ አደጋዉ ከባድ ይሆናል።

ማሳያ ሁለት፡

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦረና ቅርንጫፍ ሰራተኛ የነበረ አንድ ግለሰብ የሙስና ወንጀል ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ ተይዟል እንበል፣ተከሳሽ የፌደራል መስሪያ ቤት ሰራተኛ በመሆኑ ከዚሁ ወንጀል ጋር ተያይዞ በዚሁ ተጠርጣሪ ላይ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ስልጣኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል።ነገር ግን ወንጀሉ የተፈጸመዉ ኦሮሚያ ክልል በመሆኑና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ክልል ስላላተደራጀ በዉክልና ስልጣኑ መሰረት ጉዳዩን ለማት ስልጣኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 78/2 እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/95 አንቀጽ 2)።ይህ ፍርድ ቤት ወንጀሉ ከተፈጸመበት ቦታ በጣም ርቆ የሚገኝ በመሆኑ ተጠርጣሪዉን በቀነቀጠሮ እያመላለሱ ምርመራ ለማከናወን የሚያስችል ሆኖ አይገኝም፤ በዚህ ምክንያት መርማሪዎች እያወቁም ቢሆን ተጠርጣሪን ስልጣን በሌለዉ ፍርድ ቤት ሲያቀርቡና ፍርድ ቤቱም ጥያቄያቸዉን ሲያስተናግድ ይስተዋላል (ከኦሮሚያ የፀረ-ሙስና ዐቃቤ ህግ የተገኘ)።

## በጥቆማ ደረጃ የሙስና ወንጀል መሆን አለመሆኑን መለየት ካለመቻል ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች፣

አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣቶች ስለፈጸሙት ወንጀል ምርመራ ስለማካሄድ በህጉ የተቀመጠዉ ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ (የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዐት ህግ ቁጥር 22/2)፣ ማንኛዉም መርማሪ ፖሊስ የተሰራዉን ወንጀል በሚያዉቅበት ወይም በጥርጣሬ በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ ምርመራ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለበት በህግ ተገልጾአል (በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 22/1)፤የቀረበለት ክስ ወይም ክስ አቤቱታ የሚያጠራጥር ነዉ ብሎ ቢያስብም የጀመረዉን የምርመራ ተግባር ለመፈጸም ይገደዳል(በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 23)፡፡ይህ ድንጋጌ ከሙስና ወንጀሎች ዉጭ ያሉትን የሚመለከት ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ስራዉን እንደጀመረ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ማቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን ያለዉ የፌደራል ወይም የክልል መንግስታዊ አካል የሙስና ወንጀል ለመፈጸሙ ጥቆማ ሲደረሰዉ ወይም ወንጀሉ ለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ ሲኖረዉ ከኮሚሽኑ ዉክልና ማግኘት ሳያስፈልገዉ ምርመራዉ መጀመርና የማጣራት ሃላፊነት እንዳለበት በህግ ተደንግጓል (አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 8/2)፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰዉ ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ የሚታዩት የሙስና ወንጀሉን ለማየት ስልጣን በተሰጠዉ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ ፖሊስ የሙስናንም ሆነ ሌሎች ወንጀሎችን ለማጠራት ስልጣን የተሰጠዉ በመሆኑ በያዘዉ ጉዳይ ላይ ከምርመራ ስራ ጋር በተያያዘ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማግኘት ቢፈልግ (ለምሳሌ የምርመራ ማጣሪያ ቀነቀጠሮ) የተፈጸመዉን የወንጀል አይነት ማወቅ መቻል ይኖርበታል፤ ይህ ማለት እየመረመረዉ ያለ ጉዳይ ከሙስና ዉጭ የሆነ ደረቅ ወንጀል ከሆነ ተጠርጣሪዉን አቅራቢያዉ ወደሚገኝ ማንኛዉም ፍርድ ቤት ይዞ ሊቀርብ ይችላል፣ ነገር ግን ሙስና ሆኖ ካገኘዉ ተጠርጣሪዉን ለማቅረብና የምርመራ ማጣሪያ ቀነቀጠሮ መጠየቅ የሚችለዉ አቅራቢያዉ ወደሚገኝ ማንኛዉም ፍርድ ቤት ሳይሆን ክሱን ለማየት ስልጣን ለጠሰጠዉ ፍርድ ቤት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡ ይሁንና ጉዳዩ ገና በጥቆማ ደረጃ ላይ እያለ መርማሪዉ የወንጀሉን አይነት መለየት የሚቸገርበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ በዚህ ጊዜ ተጠርጣሪዉን አቅራቢያዉ ባለ ፍርድ ቤት ይወስዳል፣በዚህ መልኩ በተከታታይ የምርመራ ጊዜ ቀጠሮ ከፍርድ ቤት ካገኘ ቦሃላ በሂደት የሙስና

ወንጀል መሆኑን ፍርድ ቤቱ ወይም ራሱ መርማሪዉ ሲያዉቅ የተከፈተዉን የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ በማዘጋት ስልጣን ወዳለዉ ፍርድ ቤት እንደ አዲስ የሚያቀርብበት ሁኔታ በብዛት ይስተዋላል፡፡ ለማሳያ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን  የጊዜ ቀጠሮ መዝግብት እንመልከት፣

**ኬዝ አንድ፣**

ተጠርጣሪዎቹ በትምህርት ሚኒስቴር ዉስጥ መምህራን እና የነሱ ተባባሪ ናቸዉ የተባሉ ግለሰቦች ሲሆኑ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እዉቅናና ፈቃድ ዉጭ የፕላዝማ ሳታላይት ፕሮግራሞችን በመጽሀፍ መልክ አሳትመዉ በመሸጥ ለግል ጥቅማቸዉ አዉለዋል በሚል ተጠርጥረዉ   ይከሰሳሉ፤ ይህ ጥቆማ የደረሰዉ የፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ መምሪያም ተከሳሾቹን በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራ ይጀምራል፤ጉዳዩ ሰፊና ጊዜን የሚጠይቅ ሆኖ በማግኘቱም ተጠርጣሪዎቹን በአቅረቢያዉ ወደሚገኝ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ በማቅረብ የምርመራ ማጣሪያ ጊዜ ቀጠሮ ይጠይቃል፤ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ሊመረመር እንደሚገባዉ አምኖ ለመጀመሪያ ጊዜ 14 ቀን ይሰጣል፡፡ ጉዳዩ በጅምር ላይ ባለበት ሁኔታ የሙስና ወንጀል መሆን አለመሆኑን በፖሊስም ሆነ በፍርድ ቤት በኩል ለማወቅ የሚያስችል ባለመሆኑ በዚህ መልኩ ፖሊስ እየጠቀ ፍርድ ቤቱም እየፈቀደ ተጠርጣሪዎች በጊዜ ቀጠሮ ይቆያሉ፡፡በመካከሉ የሙስና ወንጀል ሊያሰኙ የሚያስችሉ ፍንጮችን ማየት የጀመረዉ መርማሪ ፖሊስ በጉዳዩ ላይ አስተያት እንዲሰጠዉ የፌደራል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ህግን በደብዳቤ ይጠይቃል፤የኮሚሽኑ ዐቃቤ ህግም የሙስና ወንጀል መሆኑን በመለየት የተጀመረዉ ምርመራ በነሱ በኩል ተጠናቆ እንዲቀርብለት በማሳሰብ አስተያየቱን በደብዳቤ ለምርመራ ክፍሉ ያሳዉቃል፤የፌደራል ፖሊስ ምርመራ ክፍልም አስተያየቱ እንደደረሰዉ በፍርድ ቤት የተከፈተዉን ጊዜ ቀጠሮ ካዘጋ ቦኋላ ተጠርጣሪዎችን ፌደራል ከፍተኛ ፍረድ ቤት እንደአዲስ በማቅረብ ጊዜ ቀጠሮ ይጠይቃል፤ ፍርድ ቤቱም የ14 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡(የጊዜ ቀጠሮ መ/ቁጥር 445/99)፤

**ኬዝ ሁለት፣**

በቦሌ ክፍለ ከተማ ዉስጥ በደንብ አስከባሪነት ይሰሩ የነበሩ 7 ግለሰቦች ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ጥቆማ የደረሰዉ የቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ግለሰቦቹን አስሮ ምርመራ ይጀምራል፤ ተጠርጣሪዎቹን ባሰረ በ48 ሰዐት ዉስጥም አቅራቢያዉ ወደ ሆነዉ የቦሌ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ የምርመራ ማጣሪያ ቀነቀጠሮ እንዲሰጠዉ ያመለክጣል፣ ፍርድ ቤቱም ለምርመራ ማጣሪያ ይበቃል ብሎ የገመተዉን 10 ቀን ቀነቀጠሮ ይሰጣል፤በ10ኛዉ ቀን ፖሊስ ምርመራዉን እንዳላጠናቀቀ ገልጾ ተጨማሪ ቀን ቢጠይቅም ፍርድ ቤቱ የፖሊስን ጥያቄ ባለመቀበል ተጠርጣሪዎች በዋስ እንዲቆዩ ሲል ያዛል፤(የጊዜ ቀጠሮ መ/ቁጥር 0170/99)፤ ፖሊስ የፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀርባል፤ የበላይ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ እየተጣራ ያለዉ ጉዳይ የሙስና ወንጀል ነዉ ካለ ቦኋላ የስር ፍርድ ቤት የጊዜ ቀጠሮ ለማየትም ሆነ ዋስትና ለመፍቀድ ስልጣኑ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ይሽራል (የጊዜ ቀጠሮ ይግባኝ መ/ቁጥር 0379)፡፡ የትዕዛዙን መሻር ተከትሎም መርማሪዉ ተጠርጣሪዎችን ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደአዲስ በማቅረብ ጊዜ ቀጠሮ ይጠይቃል፤ ፍርድ ቤቱም የ14 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መዛግብቶች ተግባራዊ ችግሩን ለማሳየት በምሳሌነት ቀረቡ እንጅ እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮችም አሉ፡፡

## ስልጣን በሌለዉ ፍርድ ቤት ከሚሰጡ ትዕዛዛት ህጋዊ ዉጤት ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ ችግሮች፣

### የመወያያ ጥያቄ፣

በእምነት ማጉደል የተከሰሰ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ስልጣን ፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 35 መሰረት ድርጊቱን አምኖ በዝርዝር አምኖ የሰጠዉን የዕምነት ቃል ዐቃቤ ህግ ክስ ሲመሰርት በማስረጃነት ምቅረብ ይችላል? የተከሳሹን የእምነት ቃል በማስረጃነት ማቅረብ ይችላል ተከሳሹ ቢቃወምስ ክሱን እያየ ያለዉ ፍርድ ቤት ምን መወሰን አለበት?

ማንኛዉንም ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ አይቶ ማንኛዉንም ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ ለመስጠት በህግ የተሰጠ ስልጣን ሊኖርዉ ግድ ይላል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ የሚታዩት የሙስና ወንጀሉን ለማየት ስልጣን በተሰጠዉ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ይህ ማለት ሙስና ወንጀሉን ክስ ወይም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማየት ስልጣን ከተሰጣቸዉ ዉጭ ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህን ጉዳይ አይቶ ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ህጋዊ ስልጣን የላቸዉም ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ የወንጀል ክስ የቀረበለት ማንኛዉም ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከማየቱ በፊት በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆን በቅድሚያ መመርመር ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ ካረጋገጠ ጉዳዩን መዝጋት ወይም ከሳሹ አካል ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ማመላከት ይኖርበታል፡፡ስልጣን ሳይኖረዉ አንድን የወንጀል ክስ ተቀብሎ ዉሳኔ ቢሰጥ ዉሳኔዉ በስልጣን ማጣት ምክንያት በበላይ ፍርድ ቤት የሚሻር ይሆናል፡፡ ፍርድ ቤቱ ከሙስና ወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ጉዳዮች ላይ ስልጣን ሳይኖረዉ ተቀብሎ ትዕዛዝ ቢሰጥ ህጋዊ ዉጤቱ ምን ይሆናል? የሚለዉን ጥያቄ የሚመልስ ግልጽ ህግ የለም፡፡ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም በተግባር ያጋጠመ ችግር ይህን ጽሁፍ ባዘጋጀበት ወቅት ማግኘት ባይችልም በሂደት አይከሰትም ብሎ መድፈር የሚቻል ባለመሆኑ ለዉይይት ይረዳ ዘንድ ማቅረቡን መርጧል፣

ነገር ግን ከላይ ኬዝ ሁለት በሚል ከቀረበዉ ማሳያ መረዳት እንደሚቻለዉ የቦሌ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሙስና ጉዳይ ተጠርጥረዉ በቀረቡ ተጠርጣሪዎች በዋስ እንዲወጡ የሰጠዉ ትዕዛዝ በሌለዉ ስልጠን በመሆኑ የሰጠዉ ትዕዛዝ በበላይ ፍርድ ቤት ሊሻር ችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ ከምረመራ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ትዕዛዝ ዉጤት አልባ ሊሆን ይችላል ወደሚል መደምደሚያ መሄድ ይቻላል፡፡

## 6. በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ሰው በዋስትና መለቀቅን በተመለከተ፣

በሙስና ወንጀል የተከሰሰ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል ከአስር አመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ በዋስትና እንደማይለቀቅ በልዩ ስነስርአት ህጉ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ማለትም ተከሳሹ በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ

ሊፈረድበት የሚችለው ከፍተኛው የቅጣት ጣሪያ ከአስር አመት በላይ ከሆነ የዋስትና መብት አይኖረውም ማለት ነው፡፡

ይሁንና በዋስትና ጥያቄ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ይግባኝ የተጠየቀው ተጠርጣሪው በዋስ እንዲፈታ በተሰጠ ውሳኔ ወይም በዋስትና እንዲያሲዝ በተጠየቀው የገንዘብ መጠን ላይ ከሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ውሳኔው ሳይፈጸም ይቆያል ማለትም ተጠርጣሪው ሳይፈታ ይቆያል ማለት ነው፡፡

ፍርድ ቤት በዋስትና ጥያቄ ላይ ተከሳሽ ላቀረበው በዋስትና የመፈታት ጥያቄ መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ያልተቃወመ ከሆነ ግን፣ ፍርድ ቤት ዋስትናውን ሲፈቅድ አብሮ ይግባኝ የሚቀርብበትን መጠባበቂያ ጊዜ መወሰን ያለበት አይመስልም፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤት አንድ ተጠርጣሪ በዋስ እንዲወጣ ቢወስን የሚከተሉትን እገዳዎች ሊያደርግ ይችላል፡፡

ተከሳሽ፣

- ከተወሰነ ክልል ውጭ እአንዳይንቀሳቀስ ወይም
- ማስረጃ ሊያጠፋ በሚችልባቸው የተወሰኑ ቦታዎች እንዳይደርስ ወይም
- በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት እንዳያደርግ ወይም
- ወደውጭ አገር እአንዳይወጣ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ከሙስና ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ተከሳሽ የተከሰሰባቸው ወንጀሎች ከአንድ በላይ ተደራራቢ ቢሆኑና፣ እያንዳንዳቸው ከአስር አመት ያልበለጠ የሚያስቀጡ ቢሆን፣ ሊኖር ስለሚችለው ሁኔታ ህጉ በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤቶች ተደራራቢ ወንጀል በሚሆንበት ጊዜ በእያንዳንዱ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊቀጣ የሚችለውን ቅጣት በመደመር ዋስትና የሚከለከልበት ሁኔታ ምክንያታዊና ተገቢነት ያለው ሆኖ ይታያል፡፡

ከዋስትና መሰጠት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ በተለይም ክስ ባልተመሰረተበት ጊዜ ተጠርጣሪው የሚቀጣው ቅጣት ምን ያህል እንደሆነ መለየት ስለማይቻል፣ የዋስትና ጥያቄው ላይ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ መስሎ ይታያል፡፡

## 7. ንብረትን ስለማሳገድና ስለመውረስ፡፡

***መወያያ ጥያቄ***

*የሙስና ወንጀል ፈጸመ ተብሎ ምርመራ የተጀመረበት የጉምሩክ ሰራተኛ ሚስት በቅርቡ በስሟ የተመዘገበ አዲስ ማርቸዲስ መኪና መርማሪው በሙስና የተገኘ ንብረት ነው እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ይተገድ፣ መኪናውንም ለጊዜው መንግስት ተረክቦ ያስተዳድረው፣ ከተሽከርካሪው አገልግሎት የሚገኝ ገቢ በባንክ እንዲቀመጥ በማለት ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ እርስዎ ዳኛ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ? በተጠየቀው መሰረት እንዲተገድ ትአዛዝ የማይሰጡ ከሆነ፣ የአግድ ትአዛዝ ለመስጠት ምን እንዲሟላ ይጠይቃሉ?*

የሙስና ወንጀል የፈጸመ ሰው በመታስር ቢቀጣም በወንጀሉ ያገኘው ጥቅም ከፍተኛ ከሆነ፣ መታሰሩ ብቻ ከወንጀል ድርጊቱ እንዲታቀብ አያደርገውም ወይም ሌሎች ሰዎች መታሰሩን አይተው ድርጊቱን ከመፈጸም እንዲታቀቡ አያደርጋቸውም፡፡ ሙስና በዋነኛነት የሚፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ነው፡፡ ስለሆነም ወንጀሉን ለመፈጸም የሚያነሳሳውና የሚያደፋፍረው ከድርጊቱ በስተጀርባ የሚገኘው ጥቅም ነው፡፡ በሙስና ወንጀል የተገኘ ጥቅም ሊወረስ ወይም ሊነጠቅ የሚያስችል ስርአት ከአለ ግን ሰዎች የሙስና ወንጀል እንዳይፈጽሙ እንዲታቀቡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ወንጀል መፈጸማቸው ከተደረሰበት ከመቀጣት በስተቀር የሚያተርፉት ነገር ስለማይኖር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በሙስና ወንጀል የተገኘ ሀብትን ለመውረስ እንዲቻል የተቀመጡ የስነስርአትና የማስረጃ ድንጋጌዎች አሉ፡፡

### ***የንብረት እግድ ትአዛዝ ማለት ምን ማለት ነው?የሚታገደው ንብረት ምን አይነት ንብረት ነው?***

ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ንብረት ማገድ በሁለት መልኩ ሊፈጸም ይችላል፡፡ እነርሱም፣

- በሙስና ወንጀል የተገኘ ነው ተብሎ በሚገመት ንብረት ላይ የሚሰጥ የአግድ ትእዛዝ (አዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 8)እና

- በሙስና ወንጀል የተገኘ ባይሆንም በተከሳሽ ስም ባለ ንብረት ላይ የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ ነው፡፡(አዋጅ ቁ 434/97 አንቀጽ 9)

**በሙስና ወንጀል የተገኘ ነው ተብሎ በሚገመት ንብረት ላይ የሚሰጥ የአግድ ትአዛዝ**

ተከሳሽ በሙስና ያገኘው ነው ተብሎ የሚገመት ንብረትን በሚመለከት በንብረቱ ላይ ያለውን መብት እንዳይጠቀምበት የሚከለክል ትአዛዝ ሲሆን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍን የመጠቀም መብት መስጠትንና ማስወገድን ይጨምራል፡፡ (አ. ቁ 434/97 አንቀጽ 2(4)፡፡ ይህ ማለት ተከሳሹ በንብረቱ ላይ የመጠቀምም፣ የማስተዳደርም ሆነ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብትን የሚከለክል ሲሆን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤት፣

1. ንብረቱን በአደራ አስቀማጭነት ይዞ የነበረ ሰው ንብረቱን እንዲለቅ፣
2. ንብረቱን ተቀብሎ የሚጠብቅ ሰው መርጦ መሾምና እንዲጠብቅ፣
3. ተቀባዩ ንብረቱን ስለሚያስተዳድርበት ሁኔታ ስልጣን መስጠት፣
4. ከንብረቱ የሚገኘውን ገቢና ትርፍ ለመሰብሰብና ገንዘቡን እንዴት ማድረግ እንዳለበት

ትአዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ (አንቀጽ 13 እና ተከታዮቹ)

ተከሳሽ በሙስና ወንጀል ያገኘው ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚቻለው እንዴት ነው?

1. በፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር በሙስና ወንጀል የተገኘ ለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ ከተወሰነ በሙስና የተገኘ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወረስ ይደረጋል፡፡ ይህ ብዙም የሚያስቸግር አይደለም፡፡
2. ይሁንና የአግድ ትአዛዝ ጠቀሜታ የሚኖረው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ተከሳሽ ንብረቱን እንዳያሸሽ ለመጠበቅ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የአግድ ትአዛዝ እንዲሰጥ ከክስ በፊትም አቤቱታ ሊቀርብ እንደሚችል በልዩ ስነስርአት ህጉ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም መርማሪው ምርመራ በተጀመረበት በማንኛውም ጊዜ የአግድ ትአዛዝ እንዲሰጥለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ይሁንና በሙስና የተገኘ ለመሆኑ ምን አይነት ማስረጃ ይዞ መቅረብ አለበት? በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2 መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት

ነው ለማለት ምርመራ በተጀመረበት ድርጊት የተገኘ ንብረት ለመሆኑ አንዳንድ አመላካች ማስረጃዎችን በማያያዝ በሙስና ወንጀል የተገኘ ነው ለማለት በቃለ መሀላ የተደገፈ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ህጉ ይደነግጋል፡፡

## በሙስና የተገኘ ባይሆንም ንብረት ስለሚታገድበት ሁኔታ

በሙስና ወንጀል የተገኘ ባይሆንም በተጠርጣሪ ስም ያለ ማንኛውም ንብረትም ቢሆን ሊታገድ ይችላል፡፡ ይሁንና የሚታገደው ንብረት በሙስና የተገኘ ስለመሆኑ መረጃ ካልቀረበበት የእግዱ ውጤት የተለየ ነው የሚሆነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርብ የተጠርጣሪ ንብረት ላይ የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ ተጠርጣሪ ንብረቱን እንዳይሸጥና እንዳይለውጥ የሚከለክል ነው፡፡ ይሁንና ተጠርጣሪው በንብረቱ የመጠቀም መብቱ አይነካበትም፡፡ (አንቀጽ 9(2)

አንዳንድ ጊዜ የሙስና ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች በፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ንብረቱ እንዳይያዝ በሌላ ሰው ስም ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ይሁንና በማስረጃ ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ከተከሳሹ በስጦታ የተሰጠ፣ በአደራ የተቀመጠ እና የተሸሸገ ገንዘብንም ቢሆን ሊታገድ እንደሚችል በህጉ ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 2(2)

በሙስና ወንጀል የተከሰሰው በወንጀሉ ማጥፋቱ ከተረጋገጠ በሙስና የተገኘው ንብረት ይወረሳል ወይም በሙስና አገኘ ተብሎ ከሚገመተው ጥቅም ወይም አደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነው መጠን ከታገደው ንብረት ላይ ተቀንሶ ወይም ተሸጦ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፡፡

ይሁንና ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ በወንጀሉ ጥፋተኛ መሆኑን ወስኖ ንብረቱን በሚመለከት ትእዛዝ ሳይሰጥ ሊቀር ይችላል፡፡ (አንቀጽ 31) እንዲህ በሆነ ጊዜ አቃቤ ህጉ ንብረቱ ላይ የውርስ ውሳኔ እንዲሰጥ ሌላ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት ያቀርባል፡፡ ፍርድ ቤቱም በህግ በተመለከተው መሰረት ጉዳዩን መርምሮ እንዲወረስ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

አንዳንድ ጊዜ በሙስና የተገኘው የማይገባ ጥቅም የአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከባንክ ከህግ ውጭ የተገኘ ብድር ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ባለ ጊዜ ክሱን የሚከታተለው አቃቤ ህግ የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት በንብረቱ ላይ ክስ እንዲመሰርት ማድረግ ይችላል፡፡ (አንቀጽ 32) ውጤቱንም እንዲከተተል በህግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል ተከሳሹ ከወንጀሉ ነጻ ነው ተብሎ በፍርድ ቤት ከተወሰነለት፣ የታገደው ንብረት ላይ ያለው እግድ እንዲነሳ ማመልከቻ ያስገባል፡፡ ፍርድ ቤቱም በንብረቱ ላይ የተጣለውን እግድ ከማንሳቱ በፊት አቃቤ ህግ አስተያየቱን እንዲሰጥ ይጠይቃል፡፡ (አንቀጽ 15(2)፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት 1) አቃቤ ህግ በስር ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ኖሮት ይግባኝ ጠይቆበት ከሆነ፣ የንብረት እግዱ መነሳቱ የይግባኝ ክርክር ውጤቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚኖረው ነው፡፡ 2) በወንጀሉ ነጻ ቢሆንም ንብረቱ እንዲመለስ በፍትሀብሄር ክርክር የማድረግ አቅጣጫ ውስጥ የገባ ከሆነም ንብረቱ ታግዶ መቆየት ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤት እግዱ ይነሳ ወይም አይነሳ ብሎ ለመወሰን የሚችለው የአቃቤ ህጉን ክርክርና መልስ ከመረመረ በኋላ ነው፡፡

አቃቤ ህጉ ክሱን ቢያነሳ ወይም ቢያቋርጥ፣ እግዱን በተመለከተ እንዲነሳ አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል ወይ በሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የእንግሊዝኛው ትርጉም ይህንን በተመለከተ ያስቀመጠው ለየት ያለ ነው፡፡ where the case is withdrawn or the defendant is acquitted or is not found guilty (art. 15(1)) የእንግሊዝኛው ምክንያታዊና አሳማኝ ይመስላል፡፡ ስለሆነም ክሱ እስከተነሳ ወይም እስከተቋረጠ ድረስ እግዱ እንዲነሳ ፍርድ ቤቱ ቢወስን ተገቢነት ያለው ነው፡፡

***<u>መወያያ ጥያቄ</u>***

ሶስተኛ ሰዎች ባልተከሰሱበትና ባልተከራከሩበት ሁኔታ በስማቸው የተመዘገበን ወይም በይዞታቸው ስር የሚገኝን ንብረት እንዲወረስ ትእዛዝ መስጠት ተገቢ ነው ወይ?

## ማስረጃን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣

## 1. <u>ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት ሀሳብ ግምት</u>

በሙስና ወንጀል ሞራላዊ ፍሬ ነገሩ ምንድነው?

ስለሙስና ወንጀል ትርጉም በተመለከትንበት ጠቅላላ ትርጉም ውስጥ «የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ» የሚል ሀረግ እናገኛለን፡፡ ይህ ማለት በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ለመሆን ወንጀሉ ታስቦ የተፈጸመ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሙስና ወንጀል ድንጋጌው በተግባር የተጣሰው በቸልተኝነት ከሆነ በሙስና ወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት አይሆንም ማለት ነው፡፡

**<u>በሙስና ወንጀል ሞራላዊ ፍሬ ነገር መኖሩን ለማረጋገጥ ምን አይነት ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል?</u>**

<u>አንቀጽ 403. **ጥቅም የማግኘት ወይም የመጉዳት ሀሳብ ግምት**</u>

«ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በአንቀጹ ውስጥ የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር(ድርጊት) እንደተፈጸመ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሶስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል»

በዚህ ድንጋጌ መሰረት፣

1. ወንጀሉ ጥቅም ለማግኘት ወይም ጉዳት ለማድረስ መሆኑ ተደንግጎ የተገኘ ከሆነ እና
2. የድርጊት ክፍሉ መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣

ሞራላዊ ፍሬነገሩ እንደተሟላ ማለትም ድርጊቱን የፈጸመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት እንዳሰበ ተደርጎ ይገመታል ማለት ነው፡፡

ይሁንና ይህ ድንጋጌ አዲስና ያልተለመደ ከወንጀል ህግ መርሆዎች ጋር የማይጣጣም እንደሆነ ተደርጎ በአንዳንድ ወገኖች ይቀርባል፡፡ ይሁንና በወንጀል ክስ ህሊናዊ ወይም ሞራላዊ ሁኔታ አለመኖሩን የማስረዳት ሸክም በተከሳሹ ላይ መጣል አዲስ ሳይሆን ቀድሞ በነበረው የወንጀል ህግ በሌሎችም የወንጀል አይነቶች ይሰራበት የነበረ መሆኑን የወንጀል ህጉን በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡

በ1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስድስተኛ መጽሀፍ በሀብቶች ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች በሚደነግገው ጠቅላላ ድንጋጌዎች ውስጥ በአንቀጽ 628 እና 641 ስርየሚከተለው ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ የድንጋጌውን ሀሳብ በግልጽ የሚያሳየው የእንግሊዝኛው ትርጉም ስለሆነ ይህንን እንመልከት፡፡

628. Unlawful or unjustifiable enrichment.

1) Where the law requires$ in order that there be an offence$ that the offender shall have acted with intent to procure the unlawful enrichment of himself or of a third person$ there is a presumption that the act was done in order to obtain a benefit or an unjustifiable advantage.

641. እምነት ስለማጉደል፣

2/ ተከሳሹ በእምነት የተሰጠዉን እቃ ሸጦ ያገኘዉ ገንዘብ ወይም በሌላ ነገር ለዉጦ የወሰደዉ ልዉጫ ወይም ለሌላ ለተወሰነ ጉዳይ የሚያገለግልና ወይም በዚሁ በአደራ ተቀብሎ በነበረዉ ነገር ሽያጭ የገዛዉም የተካዉም ሌላ አይነት እቃ ሁሉ እንደሌላ ሰዉ እቃ ይቆጠራል፡፡

3/ ተከሳሹ የተቀበለዉን እቃ ወይም የገንዘቡን ንብረት ወደራሱ ለማዛወር ያሰበበትን ወይም ባለይዞታነቱን ለራሱ ያደረገበትን ሁኔታ ወይም ይኸዉ በአደራ የተቀበለዉ ገንዘብ ወይም እቃ …… እንዲመልስ በተጠየቀ ጊዜ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ያልቻለ መሆኑን ……… ሲገነዘበዉ ይህ በእምነት የተቀበለዉ እቃ ለግል ጥቅሙ ያዋለዉ መሆኑን ሊረዳዉ ይችላል፡፡

በ1997 በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 663/2 ተመሳሳይ ድንጋጌ እናገኛለን፡፡

ወንጀል አድራጊው ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሰው ህገወጥ ጥቅም ለማስገኘት አስቦ የፈጸመው ድርጊት ወንጀል መሆኑ በህግ የተደነገገ ሲሆን ድርጊቱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የተፈጸመ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

እንዲሁም ከእምነት ማጉደል ወንጀል ጋር በተያያዘ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675(3) ከቀድሞው የወንጀል ህግ የነበረውን ቃል በቃል አስቀምጦ እንመለከታለን፡፡
«ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን እቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም እቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለው ይቆጠራል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የሞራላዊ ፍሬ ነገር አለመኖሩን የማረጋገጥ የማስረዳት ሸክም በተከሳሽ ላይ መጣል ለሙስና ወንጀል ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም አይነት ወንጀሎች ቀድሞ በነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ህግም ሆነ በአሁኑ የወንጀል ህግ የነበረ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

ይህ ማለት ግን ድርጊቱ መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣ሞራላዊ ፍሬ ነገሩ ተረጋግጧል ያለቀለት ጉዳይ ነው ማለት አይደለም፡፡ ህጉ የሚለው «ይገመታል» ነው፡፡ ግምትን በተጨባጭ ማስረጃ ማፍረስ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ ድርጊቱን ሲፈጽም የሙስና ወንጀልን ለማቋቋም የሚያስፈልገው ሀሳብ ያልነበረው መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ግምቱ ይፈርሳል፣ በወንጀልም ተጠያቂ ከመሆን ነጻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ስለሆነም ክስ ሲመሰረት ሞራላዊ ፍሬነገር አለመኖሩን የማረጋገጥ ሀላፊነት የተከሳሹ ሀላፊነት መሆኑን ብቻ በመመልከት ተከሳሹ በቀላሉ ሊያፈርሳቸው የሚችሉ ግምቶች መሆን አለመሆናቸውን በቅድሚያ መመርመርና ከዚሁ አንጻር ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ተከሳሹ በቀላሉ ማስረጃውን ማፍረስ ከቻለ የመንግስት ሀብትና ንብረት ያለአግባብ ይባክናል፣ ተከሳሽም ያለአግባብ መጉላላት፣ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብቱ ያለአግባብ ሊጎዳና ለማይገባ ወጪና ኪሳራ ሊዳረግ ይችላል፡፡

## 419. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ

የመንግስት ሰራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው፣

1. የኑሮ ደረጃው አሁን ከአለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ወይም፣
2. ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ከሚያገኘው ወይም አስቀድሞ በነበረበት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፣እና
3. የዚህ አይነት የኑሮ ደረጃው እንዴት እንደኖረው ወይም ንብረቱ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል እስራት ይቀጣል፡፡

ወንጀሉ ተፈጸመ ለማለት መረጋገጥ ያለበት ምንድነው?

የመንግስት ሰራተኛው፣

1. የኑሮ ደረጃው ከገቢው ጋር የማይመጣጠን ከሆነ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ቀላሉ ምሳሌ አሁን የሚያገኘው ገቢ ለምሳሌ ብር 1000 ቢሆንና በወር ውስጥ እያወጣ ያለው ብር 2000 ሊሆን ይችላል፡፡ እንዴት ይታወቃል? ይህንን ማስረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን በሆቴሎች በተለያዩ ማስረጃ ሊገኝባቸው በሚችሉ ቦታዎች እያወጣ ያለው ወጪ ብዙ መሆኑን ማረጋገጥ ከተቻለ ማስረዳት ይቻላል፡፡ ወይም
2. የመንግስት ሰራተኛው የሚያገኘው ወርሀዊ ደመወዝ ብር 1500 ቢሆንና፣ በመንግስት መስሪያ ቤት ከተቀጠረ አምስት አመት ቢሆን፣ በአጠቃላይ ታክስ ሳይቀነስ የሚያገኘው ገንዘብ ብር 90000 ይሆናል፡፡ ይሁንና በአምስተኛው አመት ላይ ብር 200000 ሺህ የሚያወጣ መኪና ይገዛል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች የመንግስት ሰራተኛው ያወጣው በገቢው ሊገዛ ከሚችለው በላይ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ተከሳሹን ተጠያቂ ለማድረግ ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ተከሳሹ ከገቢው ጋር የማይመጣጠን ሀብት ወይም ወጪ ህጋዊ ምንጭ እንዲያስረዳ ተጠይቆ ይህንን ማስረዳት ያልቻለ እንደሆነ ነው ወንጀሉን ፈጸመ የሚባለው፡፡

ስለሆነም ተከሳሹ የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ከመቀጠሩ በፊት ሀብት እንደነበረው ማስረዳት ከቻለ፣ ወይም የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ከተቀጠረ በኂላ ሌላ ይህንን ያህል ሀብት ጋር ሊመጣጠን የሚችል ህጋዊ የገቢ ምንጭ እንዳለው ካስረዳ ( ለምሳሌ የሚያከራየው ቤትና ገንዘቡን ከዚህ ከሚያከራየው ቤት ያገኘ መሆኑን ካስረዳ) ከተጠያቂነት ሊድን ይችላል ማለት ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ገቢውንና ወጪው አለመመጣጠኑን ማሳየት ብቻ ምርመራ ለመጀመር በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ክስ ለመመስረት ተጠርጣሪው ሌላ የገቢ ምንጭ እንደሌለው ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ተከሳሹ በቀላሉ ሌላ ህጋዊ የገቢ ምንጭ እንዳለው ማስረዳት ከቻለ ክሱ ዋጋ ያጣል፡፡

ይህ የወንጀል ድርጊት እንዳይሰራ ለመከላከል ወይም ተፈጽሞ ሲገኝም በቀላሉ ማስረጃ ለማግኘት የሀብትና ንብረት ምዝገባን ግዴታ የሚያደርግ ህግ መኖር በጣም አስፈላጊና መሰረታዊ ሲሆን፣ ይህም ሕግ ወጥቶ በፌዴራል ደረጃ የሀብትና ንብረት ምዝገባ ተጀምሮ በመካሄድ ላይ ነው፡፡

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 አንድ ሰው ከተከሳሽ ጋር ካለው ቅርበት ወይም ሌሎች ሁኔታዎች የተነሳ ለተከሳሹ ባለአደራ በመሆን አንድን ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ እንደያዘ ወይም ከተከሳሹ በስጦታ እንዳገኘ ፍርድ ቤት ካመነበት ጉዳዩን በሌላ ማስረጃ ካላፈረሰ በስተቀር ንብረቱ ወይም የገንዘቡ ምንጭ በተከሳሹ ይዞታ ስር እንደሆነ ይቆጠራል ይላል፡፡

ስለሆነም ንብረቱ በተከሳሽ እጅ ላይሆን ይችላል፡፡ ይሁንና፣

1. ተከሳሹ ንብረቱን በስጦታ መልክ ለሌላ ሰው የሰጠ መሆኑን ወይም
2. ለተከሳሹ ባለአደራ በመሆን ንብረቱ በሌላ ሰው መያዙ ከተረጋገጠ

ንብረቱ እጁ የገባው በሌላ መንገድ መሆኑን ካላስረዳ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም እንደማስረጃ ሊቆጠር ይችላል፡፡

## 2.. <u>ግብረ አበር ከክስ ነጻ ማድረግ</u>

የሙስና ወንጀልን ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ወንጀሉ ሲፈጸም የነበሩ ወይም ተሳተፊ የሚሆኑ ወገኖች ሁሉ ተጠቃሚ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀሉ መፈጸም ተደብቆ ሊቀር ይችላል፡፡ በወንጀሉ ተሳታፊ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ተጸጽቶ ሊያጋልጥ ቢፈልግ ወይም በጥቅም ግጭት ምክንያት ሊያጋልጥ ቢፈልግ እንኳን በወንጀሉ ተሳታፊ ስለሆነና ተጠያቂ ስለሚሆን ወንጀሉን ለማጋለጥ አይደፋፈርም፡፡ ስለሆነም በሙስና ወንጀል ተሳተፊ የሆነ ግብረ አበር በተለያየ ምክንያት ወንጀሉን ለማጋለጥ ቢፈልግ ከተከሳሽነት ወደምስክርነት ማዞር የሚያስችል ስርአት መዘርጋት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

1) በሌላ መልኩ ሊገኝ የማይችል ማስረጃን ለማግኘት ያስችላል፣ ስለሆነም የሙስና ወንጀሎች ተገቢ ቅጣተቸውን እአንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል፡፡
2) በሙስና ወንጀል ተሳተፊ የሆነ መረጃ በመስጠቱና እነሱን በማጋለጡ እንደማይጠየቅ የሙስና ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎች ካወቁ በመካከላቸው መተማመን እንዳይኖር በማድረግ፣ እንጋለጣለን በማለት ወንጀሉን ከመስራት እንዲታቀቡ ለማድረግ የተወሰነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በሙስና ወንጀል ተሳተፊ የሆነ ሰው ከወንጀሉ ነጻ ሊደረግ እንደሚችል በልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡

ይሁንና በተጠርጣሪው ላይ ክስ እንዳይመሰረት ሊወሰን የሚችለው በወንጀሉ ተሳተፊ የሆነው ሰው ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈጸመው ድርጊትና ስለተባባሪዎቹ ሚና ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ሲሆን፣ ከክስ ነጻ ሊያደርገው የሚችለውም ኮሚሽነሩ ወይም አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ ነው፡፡

ጠቃሚ ማስረጃ የሚባለው ምንድነው?

- የቀረበው ማስረጃ ብቻውን በቀረበው የሙስና ወንጀል ክስ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት በቂ ከሆነ ወይም፣
- ማስረጃው በመገኘቱ ሌሎች መረጃዎችን ለማግኘት መሰረታዊ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ ወይም፣
- የተገኘው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመቀናጀት የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት የሚያስችል ከሆነና ባይኖር ግን የተሟላ ማስረጃ የማይኖር ከሆነ ነው፡፡

ይሁንና በወንጀሉ ተሳተፊ የሆነው ሰው በዚህ የሙስና ድርጊት ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ሀብት ከአለ ይህንን ሀብት ወይም ንብረት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

**<u>የመወያያ ጥያቄ</u>**

ግብረአበር ሆኖ ምስክርነት በመስጠት ከተከሳሽነት ነጻ የሆነ ሰዉ ምስክርነቱን ባይሰጥ ይከሰሳል የሚለው ምስክርነቱን ግዴታ ከማስመሰሉ አንፃር ፍትሀዊ ነው ወይ?

### 3. ግንኙነትና ደብዳቤ መጥለፍ

የሙስና ወንጀል ተጎጂ መጎዳቱን በማያውቅበት ሁኔታ የሚፈጸም በመሆኑ ማስረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ለሙስና ወንጀል ምርመራ ወይም ማስረጃ ለማሰባሰብ አስፈላጊ ከሆነ በስልክ፣ በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌክትሮኒክስ፣መሳሪያ፣ በደብዳቤ የሚደረግ ግንኙነት የሙስና ወንጀልን ለመመርመርና ለመክሰስ አግባብ ባለው አካል የበላይ ሀላፊ ውሳኔ እንዲጠለፍ ሊታዘዝ እንደሚችል በህግ ተፈቅዷል፡፡ (ልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 46)

ከዚህ በተጨማሪ በካሜራ፣ ድምጽ መቅረጫ እና የመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰባሰቡ ማስረጃዎች የሙስና ወንጀል መፈጸሙን ለማስረዳት እንደማስረጃ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

### 4. ስለኮምፒዩተር ሰነድ፣

በዛሬው ጊዜ ከፍተኛ ሰነዶች በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ውስጥ የሚገኙ ሆነዋል፡፡ ግንኙነትም በኢሜይልና መሰል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚደረግ ሆኖአል፡፡ ስለሆነም በኮምፒዩተር ውስጥ የሚገኙ ሰነዶች የወንጀል ድርጊት ለመፈጸሙ በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ይሁንና በሚከተሉት ምክንያቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው ከኮምፒዩተር የሚገኝ ሰነድ ተቀባይነት የማይኖረው፣

1. በኮምፒዩተሩ ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ምክንያት በሰነዱ ላይ የሰፈረው ጽሁፍ ትክክለኛ አለመሆኑን የሚያሳምኑ በቂ ምክንያቶች መኖራቸውን ወይም
2. ኮምፒዩተሩ ስራ ላይ ባልዋለባቸው ጊዜያት በተገቢው መንገድ የማይሰራ መሆኑን ወይም ኮምፒዩተሩ በስራ ላይ ባልዋለበት ወይም ከስራ ውጭ በሆነበት ጊዜ የሰነዱን አወጣጥ ወይም ይዘት የሚያፋልስ መሆኑን፣
3. በኮምፒዩተሩ ውስጥ በተገኘ መረጃ ተጎጂ የሆነ ወገን ማሳየት ሲችል ብቻ ነው፡፡

**5. <u>ስለአስጠቂ ምስክር</u>**

በሙስና ወንጀል ስለሚያውቀው ጉዳይ ምስክርነት ይሰጥልኛል ተብሎ የተጠራ ምስክር፣ ባልተጠበቀ ሁኔታ አቃቤ ህጉ ከሚጠብቀው ውጪ ምስክርነት በመስጠት ለምሳሌ ለሚጠየቀው ጥያቄ ሁሉ «አላውቅም» በማለት ወይም ተከሳሽን የሚረዳ ምስክርነት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተከሳሽ ይመሰክርልኛል ብሎ የጠራው ሰውዬ ባልተጠበቀ ሁኔታ በራሱ በተከሳሹ ላይ ሊመሰክርበት ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ቢያጋጥም ምን ማድረግ ይቻላል?

በልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 44 የሚከተለው ድንጋጌ ተቀምጧል፡፡

1. በአቃቤ ህግ ወይም በመከላከያ ምስክርነት የቀረበ ማንኛውም ሰው በምስክርነት በተጠራበት ጉዳይ እውነቱን ለመናገር ባለመፈለግ ቀድሞ ከሰጠው የምስክርነት ቃል የሚቃረን የምስክርነት ቃል የሰጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ምስክሩን ያቀረበውን ወገን መሪ ጥያቄ እንዲጠይቅ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ መሪ ጥያቄ እንዲጠየቅ ከመፍቀዱ በፊት ተቃራኒ የምስክርነት ቃል የሰጠ መሆን አለመሆኑን ምስክሩን ይጠይቀዋል፡፡ ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን ከተቀበለ መሪ ጥያቄውን ይፈቅዳል፡፡
3. ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን የካደ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ምስክሩ ተቃራኒ ቃል መስጠት አለመስጠቱን ይወስናል፡፡

**<u>የመወያያ ጥያቄ</u>**

ይህ ድንጋጌ ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች (ዐቃቤ ህግና ተከሳሽ) በእኩልነት ማገልገል ይችላል? መልስዎ አዎ ከሆነ በተከሳሽ በኩል የቀርበ የመከላከያ ምስክር አስጠቂ መሆን አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ እንዴት መወሰን ይችላል?

## <u>ዋቢ</u>

**1. የወንጀል ህግ 1996**

2. **blacks law dictionary**
3. **የኢፌዲሪ ህገ መንግስት፣**
4. **የተሻሻለው ፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 433/97**
5. **የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97**